# ***<u>የናት ሆድ !</u>***

## ***<u>ከዓሣዬ</u>***

*የናት ሆድ ዝንጉርጉር ቡራቡሬ ወልዳ*
*የሥጋዋን ክፋይ እንዳትጥል ኣውጥታ*
*እቅፍ ድግፍ ኣርጋ ኣጥብታና ኣብልታ*
*ኣሣድጋ ነበር በማር በወተትዋ ።*
*ግና !*
*ኣለመማር ክፉ ሲባል የነበረ*
*በተማረው ብሶ ለከርሱ ኢያደረ*
*ትግሉ እንዳይጧጧፍ ትግሉ እንዳይጠነክር ጋሬጣ እየሆነ*
*ኢጅና ዳንት ሆኖ ከኢትዮጵያ ጠላቶች ኣብሮ እየወገነ*
*እልቂትን ለመፍጠር በጎሣ በሃይማኖት እየከፋፈለ*
*በባዕዳን ትዕዛዝ ለባዕዳን ጥቅም ከልቡ እየጣረ ፤*
*ለዘር ማጥፋት ፍጅት ጎራዴውን መዞ*
*ጀግንነቱን ሊያሣይ በዜጋ ደም ታጥቦ*
*መርዝ ቅርሻት ማቀርሸት ተያይዟል ደፍሮ ።*

*ኣጋር መቼ ጠፍቶ ለጎራዴ ኢጀታ*
*እራሱን በሸመው ብቸኛ ጠበቃ*
*ሥድ ሰደዱን ለቆ በእሣቱ ላንቃ*
*እንደ ጭዳ በሬ ለግንቦት ልደታ*
*ጎራዴ ኣሥመዝዞ ኣንገትዋን ሊያሥመታ*
*ጽዋውን ኣጋጭቷል !*
*ሻምፓኙንም ከፍቷል !*
*ኢትዮጵያ እንደ ሃገር እንዳትኖር በካርታ*
*ብትንትኗ ወጥቶ እንድትከሰም ጠፍታ ።*

*ተቃዋሚ ተብየው የዲያስፖራ መንጋ*
*የምንሣንቶን ድቅል መርዙን እየበላ*
*ሆኖ ለወያኔ ጋሻና መከታ እንዲሁም ከለላ*
*ሃቀኛን ድርጅት እያከቸለቸለ ቢፏልል ቢያቅራራ*
*ወይ ፍንከቻ ! ወይ ንቅንቅ !*
*ጀግና ሕይወቱን ሰጥቶ ከንዱን ሣይንተራሥ*
***ሃገርማ ኣትወድቅም !***
***ሃገርማ ኣትሞትም !***
*የመጣው ቢመጣ ሰማይ ቢደረመሥ*
***በክብር ትኖራለች ! እሥከወድያኛው ድረሥ !!!***
*ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር !*

*June 22/2014 GC*